የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፸
አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year, No.70
ADDIS ABABA 22nd July, 2020

ማውጫ

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፲፯/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጂቡቲ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በወንጀል የሚፈለጉ ሰዎችን አሳልፎ ለመስጠት የተደረገው ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ...............................................ገጽ ፲፪ሺ፮፻፺፭

Content

Proclamation No. 1217/2020

Extradition Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Djibouti Ratification Proclamation ……………………………Page 12695

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፲፯/፪ሺ፲፪

**በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጂቡቲ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በወንጀል የሚፈለጉ ሰዎችን አሳልፎ ለመስጠት የተደረገውን ስምምነት ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጂቡቲ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል በወንጀል የሚፈለጉ ሰዎችን አሳልፎ የመስጠት ስምምነት መጋቢት ፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመ በመሆኑ፤

ስምምነቱን ማጽደቅ ወንጀል ፈጽመው የኮበለሉ ግለሰቦችን ለፍርድ ለማቅረብ የሚያስችል በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የህዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ሰኔ ፲፰ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም በአካሄደው መደበኛ ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ

**PROCLAMATION No. 1217/2020**

**A PROCLAMATION TO RATIFY THE EXTRADITION AGREEMENT BETWEEN THE GOVERNMENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA AND THE GOVERNMENT OF THE REPUBLIC OF DJIBOUTI**

**WHEREAS** the Extradition Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Djibouti has been signed in Addis Ababa, on the 17th day of March, 2017;

**WHEREAS** ratifying the treaty enables to bring fugitives to justice;

**WHERE AS,** the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified the said Agreement at its session held on the 25th day of June , 2020.

**NOW,THEREFORE**, in accordance with Article 55

መንግሥት አንቀጽ ፶፭(፩) እና (፲፪) መሠረት የሚከተለው ታውጇል።

**፩. <u>አጭር ርዕስ</u>**

ይህ አዋጅ "በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጂቡቲ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል የተደረገው በወንጀል የሚፈለጉ ሰዎችን አሳልፎ የመስጠት ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፪፻፲፯/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል።

**፪. የ<u>ስምምነቱ መፅደቅ</u>**

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግስት እና በጂቡቲ ሪፐብሊክ መንግስት መካከል መጋቢት ፰ ቀን ፪ሺ፱ ዓ.ም በአዲስ አበባ የተፈረመው በወንጀል የሚፈለጉ ሰዎችን አሳልፎ የመስጠት ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል።

**፫. <u>የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ኃላፊነት</u>**

የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ከሌሎች የመንግስት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱን የማስፈጸም ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል።

**4.<u>አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ</u>**

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል::

**አዲስ አበባ ሐምሌ ፲፭ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**
**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**
**ፕሬዚዳንት**

(1) and (12) the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows:

**1. <u>Short Title</u>**

This Proclamation may be cited as the "Extradition Agreement between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Djibouti Ratification Proclamation No.1217/2020".

**2. <u>Ratification of the Agreement</u>**

The Extradition Agreement signed in Addis Ababa on the 17th day of March, 2017 between the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia and the Government of the Republic of Djibouti is hereby ratified.

**3. <u>Responsibility of the Attorney General</u>**

The Attorney General of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is hereby authorized to follow up the implementation of the Agreement in collaboration with other government organs.

**4. <u>Effective Date</u>**

This Proclamation shall come into force up on publication in the Federal Negarit Gazeta.

**Done at Addis Ababa, this 22nd day of July 2020**

**SAHLEWORK ZEWDE**
**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**